# የበላይ ተቆጣጣሪ የራስ ግምገማ መመሪያዎች

ለዚህ የራስ ግምገማ እንደ መነሻ የበላይ ተቆጣጣሪው ቢሮ ሊገመገምባቸው የሚገቡ የተወሰኑ መርሆዎችን ለይቻለሁ። እነዚህ መርሆዎች ለውሳኔዬ በመረጃ ሰጪነት ከማገልገላቸውም በተጨማሪ ቦርዱ የተቀበለውን የፖሊሲ አስተዳደር በተመለከተ ተመራጭ አሰራሮችን ያጣቀሱ ናቸው፥

1. የበላይ ተቆጣጣሪ እንደመሆኔ ስራዬን የሰራሁት ቦርዱ በፖሊሲው ውስጥ በተቀመጡት በግልጽ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ አፈጻጸሜን ይገመግማል በሚል እምነት ላይ ተመስርቼ ነው።

2. አንደ የበላይ ተቆጣጣሪ ያደረግኳቸው ድርጊቶች ቦርዱ ለዋና ተቆጣሪ ቢሮው ቦርዱን ሊያጋጥመው የሚችል ውጫዊ ጫናን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ለፖሊሲዎቹ የትኛውንም ትርጓሜ እንዲመርጥ የሰጠውን መብት ከመረዳት ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው።

3. ለጥሩ የፖሊሲ አስተዳደር ቦርዱ ያለውን ቁርጠኝነት እደግፋለሁ፣ አበረታታለሁ እንዲሁም አመሰግናለሁ። የቦርዱ አመራር ዝቅ ተደርጎ እንዳይታይ ለማድረግ በትጋት ስሰራ ቆይቻለሁ፤

4. ለቦርድ ፖሊሲ አማራጮችን እንዳዘጋጅ በምጠራበት ወቅት የእነዚህን አማራጮች አንድምታዎች በግልጽ የማብራራ ከመሆኑም በተጨማሪ ይህን የማደርገው ያለ ምንም አድልዎ ነው። አስተያየቶቼን በማካፍልበት ጊዜ መግለጫዎቼን በግልጽ ለይቼ አስቀምጣቸዋለሁ።

5. ለቦርዱ መረጃ በማዘጋጅበት ወቅት ቦርዱን አንድን መረጃ ለሌላ አሳስቶ እንዳይጠቀም ለማድረግ ለክትትል የሚያገለግል መረጃን፣ ለቦርዱ የውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆነ መረጃን እና ድንገተኛ መረጃን ለያይቼ አቀርባለሁ።

6. ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ከተሰጠኝ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ እነዚያን ውሳኔዎች ወደ ቦርዱ ከመመለስ ወይም ምርጫዎቹ እንዲጸድቁ ከማድረግ ይልቅ ውሳኔ ለማሳለፍ እጥራለሁ።

እነዚህን መርሆዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ከዚህ በታች የቀረበውን መረጃ ቦርዱ እንዲያጤነው ሰብስቤያለሁ። 1

# አሳማኝ ትርጓሜዎች እና የተሳኩ ውጤቶች ማስረጃ

## RI.1 - ዕኩልነት

ግብ፥ ይህን የ21/22 SY የመጨረሻ መግለጫ ማሟላት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሳካል፥

1. ማዕከላዊ ጽህፈት ቤትን መልሶ ማዋቀርን እና በDPS ውስጥ በሚገኙ በብዙ የተለያዩ ቡድኖችና በተለያዩ አባላት መከፋፈልን ጨምሮ ቢያንሱ ሁለት የሚለያዩ/የሚነጣጠሉ ሲስተሞች/ስርዓቶች ሲለዩ። እነዚህን ስርዓቶች መለያየት በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ ብዙ የተለያዩ ቡድኖችን የሚያካትት እና መለያየቱ ከግዛት ደንቦች እና/ወይም ፖሊሲዎች ጋር የሚተሳሰር ከሆነ ስርዓቶቹን ወዲያውኑ መተካትን ሊጠይቅ የሚችል በመሆኑ ምክንያት ይህ አሳማኝ መደበኛ መለኪያና የሥኬት ደረጃ ነው። ዲስትሪክቱ ወረርሽኙ ካደረሰበት ተጽእኖዎች እያገገመ እንደመሆኑ የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞችን መልሶ ማደራጀት ያስፈለገው በክፍሎች መካከል ያሉ መከማቸቶችን ለማስቀረት እና ሀብቶችን በትምህርት ቤት ደረጃ ለማቅረብ ነው።
2. በሴፕቴምበር 2022 ዓ.ም በሰው ሀብት በተሰሩት የመጀመሪያ ይዞ መቀጠያ ስሌቶች ላይ ተመስርቶ በቆዳ ቀለም የተለዩ አስተማሪዎች እና የብዙ ቋንቋ አስተማሪዎች በDPS ውስጥ ከሌሎች አስተማሪዎች ጋር በተመሳሳይ መጠን እንዲቀጥሉ ሲደረግ። ብሔራዊ ሒደቶች መምህራን በአስደንጋጭ መጠን ሙያቸውን እየተዉ/እየለቀቁ እንደሚገኙ የሚያሳዩ በመሆኑ ይህ አሳማኝ መለኪያና ኢላማ ነው።

**ምክንያት፥** ይህ የአሰራር መዋቅሮችን ቀጣይነትና ወጥነት ባለው አኳኋን ለመለያየት ታስቦ የተዘጋጀ አሳማኝ ትርጓሜ ነው። አሁን እየሰራን እና እየኖርን የምንገኝበትን ስርዓት የፈጠረው ለክፍለ ዘመናት የዘለቀው ማግለልና ጭቆና ነው። እነዚህን ከዘር አድልዎ ጋር የተቆራኙ ስርዓቶችና መዋቅሮች ነጥሎ ማውጣት የሁሉንም ሰራተኞች የማያቋርጥ ጥረት ይፈልጋል።

**ግብ፥** በትምህርት ቤታችን ስርዓት ውስጥ ያሉ ያልተቋረጡና ሥር የሰደዱ የጭቆና ስርዓቶች ነጥሎ በማውጣት የበለጠ የዕኩል ተማሪ፣ ቤተሰብና የቡድን አባላት ተሞክሮዎችን መልሶ መገንባት።

### 1. ነጥሎ ለማውጣት ተለይቶ የተቀመጠ የቦርድ የቅሬታ አቀባበል መዋቅር

ሀ. የትምህርት ቦርዱ በሚከተሉት ከታጠረ የአስተዳደር ሞዴል ለመውጣት የሚያስችል ውሳኔ አሰጣጥ አዘጋጅቷል፥

i. ከበላይ ተቆጣጣሪው ጋር ለመግባባት ሲባል ውሳኔዎችን ማሳለፍ፣

ii. በትምህርት ቦርዱና በበላይ ተቆጣጣሪው እንዲሁም በሰራተኞች መካከል ያሉ ግልጽ ያልሆኑ የሥራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች፣

iii. በበላይ ተቆጣጣሪው ሰራተኞች እና በትምህርት ቦርዱ መካከል የሚደረግ ግልጽ ያልሆነ ግንኙነት፣

iv. የትምህርት ቦርዱ የሚተዳደርባቸው ፖሊሲዎች እና የበላይ ተቆጣጣሪው የአስተዳደር ፖሊሲዎች በግልጽ አለመለያየት፣ እና

v. ግልጽ ያልሆነና ወጥነት የሌለው የበላይ ተቆጣጣሪው የአፈጻጸም ግምገማ መስፈርት።

2

### በውጤቱ የተከተለ እርምጃ፥ *ወደ ፖሊሲ አስተዳደር መሸጋገር*

a. ወደ ፖሊሲ አስተዳደር ለመሸጋገር ጥቅም ላይ የሚውለውን ቴምፕሌት በተመለከተ ውይይቶችን ማካሄድ ለመጀመር ከኮሎራዶ የትምህርት ቤት ቦርዶች (Colorado Association of School Boards) ጋር ውል ተፈጽሟል።

b. የትምህርት ቤት ቦርዱን ወደ ፖሊሲ አስተዳደር መሸጋገር ለመደገፍ ዲስትሪክቱ የሚከተለው ኃላነት የተሰጠው የአስተዳደር ኦፊሰር ቀጥሯል፥

ሀ. ለትምህርት ቤት ቦርዱ እስከ ሕዳር 2021 ዓ.ም ድረስ የሚከተሉትን የያዘ የፖሊሲ መመሪያ በማዘጋጀት ረገድ መርዳት፥

i. የቦርድ-የበላይ ተቆጣጣሪ ግንኙነት ፖሊሲዎች

ii. የአስተዳደር ሂደት ፖሊሲዎች
iii. የመጨረሻዎች ፖሊሲዎች፣ እና
iv. iv. የአስፈጻሚ ገደብ ፖሊሲዎች

b. በሜይ ወር 2022 ዓ.ም በፖሊሲ አስተዳደር ስር እንደ ተቆጣጣሪ ኤክስፐርት ሆኖ የሚያገለግል የአስተዳደር ስርዓቶች የሙያ የምስክር ወረቀት ማግኘት
c. የጸደቁ ፖሊሲዎችን በማሟላት ጉዳዮች ላይ ለትምህርት ቦርዱ ድጋፍ ማድረግ

c. የከፍተኛ አመራር ቡድንን ግንኙነት ከፖሊሲ አስተዳደር ጋር የተስማማ እንዲሆን የሚያደርጉ የግንኙነት/ተግባቦት የሚጠበቁ ሁኔታዎች ተዘጋጅተዋል። በአሁኑ ሰዓት የፖሊሲ አስተዳደር በከፍተኛ የአመራር ስብሰባዎች ላይ መደበኛ አጀንዳ ነው። የግንኙነት ፕሮቶኮሎች በተለያዩ አጋጣሚዎችና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለSLT ተገልፀዋል።
d. ቦርዱ አሁን የሚጠብቃቸውን ሁኔታዎች ለየበላይ ተቆጣጣሪው በጽሁፍ ፖሊሲዎች ይገልጻል
   ሀ. ከመጨረሻዎችና የአስፈጻሚ ገደብ ፖሊሲዎች ጋር በተሳሰሩ ውጤቶች አማካኝነት የበላይ ተቆጣጣሪውን ግምገማ በተመለከተ ግልጽ የሚጠበቁ ሁኔታዎች ተዘጋጅተዋል።

## 2. ነጥሎ ለማውጣት ተለይቶ የተቀመጠ የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት መዋቅር፥

a. የማዳመጥና ትምህርታዊ ጉዞ፣ እና የERS ሪፖርት በአሁኑ የጽህፈት ቤቱ መዋቅር ላይ የሚከተሉት መፍትሄ ማግኘት ያለባቸው ተግዳሮቶች እንዳሉ አመልክተዋል፥
   i. በማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ምድቦች ውስጥ ያለ የተደራረበ መዋቅር
   ii. በትምህርት ቤቶችና የዲስትሪክት ጽህፈት ቤት ቡድኖች የሥራ ድርሻ ላይ ግልጽነት አለመኖር
   iii. የትምህርት ቤት ድጋፍ በአብዛኞቹ ወሳኝ ቅደም ተከተሎች ዙሪያ ለሚደረግ ስትራቴጂያዊ ድጋፍ አጽንኦት አለመስጠት
   iv. ጠንካራ የዲስትሪክት ስርዓቶች ወጥነት ባለው መልኩ ወደ ጠንካራ የትምህርት ቤት አሰራሮች አለመተርጎም
   v. በመምሪያዎች መካከል ያለውን ተደራራቢ፣ በአብዛኛው ያልተቀናጀ ድጋፍ ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ግልጽነት ማስፈለግ
   vi. የዓመታዊ ዕቅድ እና የበጀት ዝግጅት ሒደቶች በአሁኑ ወቅት ሀብቶች በማዕከልና በትምህርት ቤቶች ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያደርጉ አለመሆን

## *በውጤቱ የተከተለ እርምጃ፥ ማዕከላዊ ጽህፈት ቤትን መልሶ ማደራጀት፥*

a. የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት የስራ ምድቦች ፈርሰው ትምህርቶችን እና ትምህርት ቤቶችን በተሻለ ሁኔታ በሚያስማማ በአዲስ ሞዴል ተተክተዋል። በተጨማሪም ትምህርትን የጋራ ለማድረግ ሲባል ትምህርት ቤቶች ሰፊ የተለያየ የትምህርት ቤቶች ቤተሰብን በሚይዙ ትብብሮች ድጋሚ ተዋቅረዋል። ይህ በትምህርት ቤቶችና የዲስትሪክት ጽህፈት ቤት ቡድኖች የሥራ ድርሻ ላይ የበለጠ ግልጽነት ከመፍጠሩም በተጨማሪ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት በመምሪያዎች መካከል በተሻለ ሁኔታ እንድንሰራ ያስችለናል።
b. የሥትራቴጂያዊ እቅድ ዝግጅት ጽህፈት ቤት አሁን በሰራተኞች ኃላፊ ጽህፈት ቤት ውስጥ ተካቶ አሁን የዲስትሪክቱን እጅግ አስፈላጊ ቅደም ተከተሎች ከሚይዙት የዲስትሪክቱ የመጨረሻ መግለጫዎች ጋር እንዲስማማ ተደርጓል።
c. በማዕከላዊ ጽህፈት ቤት መምሪያዎች ውስጥ የነበረው ተደራራቢ ድጋፍ ከፍተኛ ግልጽነትን በሚያሳካ መልኩ መፍትሄ አግኝቷል።
d. አዲሱ የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት መዋቅር በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ተገልጿል፤ **05.12.2022 ED Org Chart።**
e. ከሽግግር አማካሪ ቡድን ጋር ስብሰባ አካሂጃለሁኝ። በዚህም 60 አባላትን የሚይዘው ይህ ቡድን ከሶስት ሰብሳቢዎች ጋር በመሆን **10 የቅደም ተከተል መግለጫዎችን** ለመለየት ከኦክቶበር እስከ ዲሴምበር ድረስ ሰርቷል። የሽግግር ቡድኑ ከጁላይ እስከ ኦክቶበር መጀመሪያ ካካሄድኩት አጠቃላይ **የማዳመጥና ትምህርታዊ ጉብኝት** የተገኙ ሀሳቦችን መሰረት አድርጎ ነበር። 10ሩ የቅደም ተከተል መግለጫዎች በቀጣይ ዲስትሪክቱ ስትራቴጂያዊ ፍኖተ ካርታውን ለመተግበር በሚሰራበት ወቅት ለማደርጋቸው ጥረቶች በመመሪያነት ያገለግሉኛል።

3. ነጥሎ ለማውጣት ተለይቶ የተቀመጠ የልዩ ትምህርት ስርዓቶች

a. ተጽእኖ ፈጣሪ ፍላጎቶች (AN) ያሏቸው ተማሪዎች እና ለብቻ የተዘጋጁ የትምህርት ቤት መቼቶች

i. የተጽእኖ ፈጣሪ ፍላጎቶች ፕሮግራም

በAN ማዕከል ፕሮግራም ውስጥ ለተካተቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥቁርና ጠይም ተማሪዎች ምላሽ ለመስጠት ይህ ለመምህራን በደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች ባህሪያትን እንዴት እንደሚያስተናግዱ በተመለከተ ጠንካራ የሙያ ልማት እንዲተካ እመክራለሁ። ዚህ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ፍላጎቶችን በIEPs እንዲገመግሙ እና ተማሪዎችን የበለጠ አካታችና ምላሽ ሰጪ በሆነ መቼት ለሚሰጥ የጠቅላላ ትምህርት ፕሮግራም ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ጠንካራ የባህሪ እቅዶችን እንዲያዘጋጁ ድጋፍ አደርጋለሁ።

1. ይህ ስርዓት በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ጨቋኝ እንደሆነ እገነዘባለሁ፥
    a በLRE3 AN ማዕከላት ውስጥ ባሉ የተለየ ቀለም ባላቸው ተማሪዎች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ የሚፈጥር በመሆኑ፣
    b ከAN ወደ M/M የሚሸጋገሩ ወይም “የሚወርዱ” ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ
    c የተመራቂ መጠን እና/ወይም በወቅቱ ተመራቂ መጠን ያልተመጣጠነ በመሆኑ
2. የLDT - ቦታ መወሰኛ ሂደት
3. የማዕከል ምደባዎች- አጠቃላይ - በትምህርት ቤት መካተትና ከጠቅላላ ትምህርት ተማሪ እኩዮች ጋር በመገናኘት ላይ አለመመጣጠን ይፈጥራሉ

ii. በDPS ለብቻው ተለይቶ የተዘጋጀ የትምህርት ቤት ፕሮግራም

የአሁኑን በBarrett ከSierra ጋር ተደርጎ የበረውን ውል አቋርጬ በዲስትሪክት የሚካሄድ የልዩ ትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅቻለሁ

1. ቀጣይነት ያላቸው የውል ግዴታዎች አለመሟላት ትምህርታቸውን በBarrett በሚገኘው በSierra School እየተከታተሉ የሚገኙ የDPS ተማሪዎች ከጥራት በታች ፕሮግራም እንዲከታተሉ ማድረጉን እና ይህም በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዲስትሪክት የሚካሄድ እራሱን የቻለ ፕሮግራም እንዲዘጋጅ እቅድ አቅርቢያለሁ።
2. ያልተሟሉ የውል ግዴታዎችን የተመለከቱ ልዩ ስጋቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ያጠቃልላሉ፥ ተገቢ የገደብ አሰራሮችን መጠቀምን፣ ለአእምሮ ጤና ሰራተኞች ስልጠና መስጠትን፣ የሰራተኞች በስራ ላይ አለመገኘት/የሥራ መደቦች ክፍት መሆንን፣ የዲስትሪክት ፖሊሲና ሥነ ሥርዓቶች አለመሟላትን፣ ያለ በቂ ምክንያት ሪፖርት ማድረግን፣ የዛቻ ግምገማን፣ የትምህርት ክሬዲቶች ለማጠናቀቅ ድጋፍ ማድረግን፣ ዲፕሎማዎች እና የተማሪና ፕሮግራምን የተመለከቱ ስጋቶችን ለሚመለከተው የዲስትሪክት ሰራተኛ ማሳወቅን።
3. በተጨማሪም የአሁኑ በDPS የሚካሄድ ፕሮግራም እቅድ ለተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶች ድጋፍ የሚያደርጉ እና ዲስትሪክቱ የተማሪ ምደባ ግዴታዎችን በማያሟላበት ጊዜ የሚከተልበትን የህግ ስጋት ለማቅለል የሚረዱ ተጨማሪ ሰራተኞች ምደባን ያጠቃልላል።
   በተጨማሪም ከቡድንና ፕሮግራም የባህል ስራ ጎን ለጎን ለሰራተኞች የሚሰጡ ተጨማሪና የታሰበባቸው የሙያ ትምህርት እድሎች በዝቅተኛ ደረጃ እንክብካቤ ምክንያት ለተሸጋገሩ ተማሪዎቻችን የሚሰጠውን ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲደግፉ ለማድረግ ተጨማሪ ግብዓቶችን ይፈልጋሉ።
4. Colorado ከፍተኛ ደረጃ እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ድጋፍ ለማድረግ ያሉት አማራጮች በእጅጉ ውሱን ናቸው። ዲስትሪክቱ ከመላው የግዛቱ ዲስትሪክቶች የሚመጡ ተማሪዎችን ሪፈር ለማለት በጠቅላላው 16 በቀጥታ ተደራሽ የሆኑ አገልግሎት መስጫዎችን ለማቋቋም አቅዷል።
5. የቀን ህክምና ፕሮግራሞችን ጨምሮ አገልግሎት መስጫዎች ሪፈር ለተባለ ምደባ ተማሪዎችን የሚመርጡበት አማራጭ አላቸው። ይህ ለተማሪዎች ተገቢውን ፕሮግራም በማግኘት ላይ መዘግየቶችን ከመፍጠሩም በተጨማሪ FAPE እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል። በተጨማሪም የውጭ አገልግሎት መስጫዎች ተማሪዎችን መቼ እንደሚያስወጡ መወሰን የሚችሉ ከመሆኑም ባለፈ ማድረግ የሚበቅባቸው ለዲስትሪክቶች ለተማሪዎች ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟላ ተገቢ ምደባ እንዲፈልጉላቸው

የ30 ቀናት ማስታወቂያ መስጠት ብቻ ነው። ይህ ማስታወቂያ በአብዛኛው ተማሪዎችን ያለ ምደባ የመቅረት እና ወደ ሌላ አማራጭ ደካማ ሽግግር የማድረግ ስጋት ላይ ይጥላል።

### ለ. የክፍል 504 የፕሮግራም ልዩነት

**አጠቃላይ መግለጫ፥** ክፍል 504 የ1973 የማቋቋሚያ ሕግ የፌደራል ሕግ ነው። ህጉ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ዕኩልነት መሰረት የጣለ የፍትህ ብሄር መብቶች ህግ ሲሆን ትኩረት የሚያደርገው አለማግለል ላይ ነው። ህጉ አካል ጉዳተኝነትን መነሻ አድርጎ የሚደረግ የትምህርት ፕሮግራሞችና ስራዎች ተደራሽነትና ተሳትፎ መንፈግን ይከለክላል። እኩል የመሳተፍና የመጠቀም እድል ለማግኘት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ይህን ደረጃ የሚመጥኑ አገልግሎቶች እና/ወይም አቅርቦቶች፣ በተመሳሳይ እድሜ ላይ የሚገኙ የጠቅላላ ትምህርት እኩዮቻቸው የሚጫወቱበትን የመጫወቻ ሜዳ ማግኘት አለባቸው።

i. ክፍል 504 የገንዘብ ድጋፍ የማይደረግለት ኃላፊነት ማለትም ብቸኛ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በዲስትሪክት ጠቅላላ የገንዘብ ድጋፎች በኩል ሲሆን በዲስትሪክቱ ውስጥ ትግበራውን የሚደግፉ ምንም ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች የሉም።
   1. የክፍል 504 የሥነ ሥርዓት መመሪያን፣ ታስቦበት የተዘጋጀ እቅድና ድጋፍን በአግባቡ ለመከተል ያስችለን ዘንድ
      የትምህርት ቤት መሪዎች የልጆች ማግኘት ግዴታችንን ለመደገፍ ተገቢውን FTE የማካተት ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። ይህ በመኸር ወቅቱ የማስተካከያ ጥያቄዎች ወቅት
      በአብዛኛው ከግምት ውስጥ ያልገባና ያልታየ ከመሆኑም በተጨማሪ በመጀመሪያው የFTE ዕቅድ ዝግጅት ውስጥም አልተካተተም።
   2. የልዩ አገልግሎት አቅራቢዎች በማዕከላዊ FTEያቸው አማካኝነት ለአገልግሎቶች ድጋፍ ይሰጣሉ። በአሁኑ ወቅት በመኸር ወቅቱ ማስተካከያ ወይም ተጨማሪ ግብአቶች አማካኝነት ለሁሉም የማዕከላዊ የሥራ መደቦች የFTE ማስተካከያዎችን የሚደግፉ ምንም አሰራሮች የሉም።
   3. በአሁኑ ወቅት በዲስትሪክቱ ውስጥ ባሉ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የክፍል 504 አስተባባሪዎችን ለመደገፍ ዲስትሪክቱ ያለው አንድ የክፍል 504 ስፔሻሊስት ነው። የህጻን ማግኘት እና የክፍል 504 አሰራር ተገቢ ትግበራን ለማረጋገጥ እና ማግለልን ለመከላከል ተጨማሪ ማዕከላዊ ድጋፍ ታሳቢ መደረግ አለበት።

ii. የክፍል 504 ትግበራ ስጋቶች
   1. ሁሉም የክፍል 504 አስተባባሪዎች በመማሪያ ቦታ ላይ ያልተማከለ የክፍል 504 ስልጠና አልወሰዱም።
   2. ትምህርት ቤቶች ሁለት ፍቃድ ያላቸው እና በሳምንት በትንሹ 4 ቀናት በትምህርት ቤት ህንጻ ውስጥ ተገኝተው የሚሰሩ አስተባባሪዎችን አይመድቡም።
   3. ሁሉም የ504-ብቁ ተማሪዎች የሥነ ሥርዓት መስፈርቶች - የተፈረመ ስምምነት/ፍቃድ፣ ግምገማ/ድጋሚ ግምገማ እና ዓመታዊ ስብሰባ የላቸውም።
   4. ለልዩ ትምህርት ተማሪ ላይ ግምገማ ማካሄድ ወይም ቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ (PWN) እና በክፍል 504 ስር ተማሪን መገምገም አለመቻል
   5. የልጅ ማግኘት ግዴታን ለማስቀረት ወይም ለማዘግየት ተማሪዎችን ወደ MTSS ማስገባት
   6. ተማሪዎችን ወደ መሸጋገሪያ ትምህርት ቤቶች ማስገባት
   7. የአሁኑ የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲ የተሻሻለ አሰራርን እና የወላጅ የተገቢ አሰራር የማግኘት መብቶችን በሚደግፍ መልኩ መሻሻል ያስፈልገዋል።
   8. የወላጅ፣ ተማሪ፣ ሰራተኞች እና የትምህርት ቤት መሪ የክፍል 504 አላማን እና መሰረትን መረዳት፥ ህጉ የተዘጋጀው ችሎታና ልህቀትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ሳይሆን የትምህርት ተደራሽነትና ዕድል እኩል መብቶችን ማግኘት ለሚያስፈልጋቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ነው። ቡድኖች ለቡድኖች ያልተገቡ አገልግሎቶችና አቅርቦቶችን እንዲያዘሩና ጫና እንዲያደርጉ የሚፈቅዱ ከሆነ በሁሉም ተማሪዎች እኩልነት ላይ ተጽእኖ እንፈጥራለን።

በተጨማሪም፣ ከጥቁር ልህቀት ውሳኔ ጋር በማጣጣም በቀደሙ አያቶቼ የተለዩትን የቀድሞ ስርዓቶችን መለየቴን እና ነጥዬ ማውጣቴን እቀጥላለሁ።

**የጥቁሮች ልህቀት ውሳኔ (BER)**

**የሚከተሉት ስርዓቶች ተነጥለው መውጣት እንደሚያስፈልጋቸው ተለይተዋል፥**

1. በዲስትሪክታችን ውስጥ ባለቻው ተሰጥኦ፣ ስጦታዎች፣ ችሎታዎች እና የዕለት ከእለት ተሞክሮዎች ላይ ካለው አድልዎ ጋር የተቆራኙትን ጨምሮ በጥቁር ተማሪዎች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ ወደሚያደርሱ ድርጊቶችና ባህሪያት የሚመሩ የአስተሳሰብ ግድፈቶች
2. ከልክ ባለፈ መልኩ ጥቁር ተማሪዎችን ለሥነ ምግባር እርምጃ የሚለዩ ተቋማዊ መዋቅሮችና ሥነ ሥርዓቶች 3. ጥቁር ተማሪዎችን ለጠንካራ የትምህርት ተሞክሮዎች አሳንሰው የሚለዩ ተቋማዊ መዋቅሮችና ሥነ ሥርአቶች።

**ምላሽ፥** ከጥቁሮች ልህቀት ውሳኔ (BER) ጋር በተጣጣመ መልኩ እና የአመለካከት ክፍተቶች መፍታትን ለመደገፍ ቡድኔ የሚከተሉትን አዘጋጅቷል፥

- ሁሉንም የDPS የቡድን አባላት በትምህርት ውስጥ ስላሉ አፋኝ እና አካታች ልምምዶች ለማስተማር ቀጣይነት ያለው ግልጽ ያልሆነ አድልዎ ማስተማር
  - የእኩልነት ተሞክሮ ሞጁሎች፣ ለባህል ምላሽ ሰጪ ትምህርት፣ የDPS ክህሎቶች
- የጥቁር ልህቀት የሚከተሉትን ለማድረግ አቅዷል፥
  - ታሪካዊ ኢ-ፍትሀዊነትን የሚያራምዱ አዋቂ ሰዎች አስተሳሰቦችና ልምዶችን መርምሮ መፍትሄ ለመስጠት
  - ጥቁር የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ጨምሮ - የጥቁር ቤተሰብ ተሳትፎን ለማጠናከር
  - ተመራጭ አሰራሮችና ስትራቴጂዎችን ለመለየት በሚካሄዱ ስብሰባዎችና ቃለ መጠይቆች አማካኝነት የሚገኙ የBEP Learning Cohort ውጤቶችን ለውጤታማ ትግበራ ጥቅም ላይ ለማዋል

**የLGBTQ+ ኢኒሺየቲቮችና ድጋፎች**

**የሚከተሉት ስርዓቶች ተነጥለው መውጣት እንደሚያስፈልጋቸው ተለይተዋል፥**

1. የLGBTQ+ ማንነቶችን በተመለከተ ያለው ታሪካዊ ዝምታ እና ከትምህርት ቤት ስርዓቶች ውስጥ መሰረዝ
2. የLGBTQ+ ተማሪዎችን እና የቡድን አባላትን በDPS የመረጃ ቋት ሲስተሞች፣ ሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ቤት ህንጻ መሰረተ ልማት ውስጥ አለማካተት
3. በዲስትሪክታችን ውስጥ ባለቻው ተሰጥኦ፣ ስጦታዎች፣ ችሎታዎች እና የዕለት ከእለት ተሞክሮዎች ላይ ካለው አድልዎ ጋር የተቆራኙትን ጨምሮ በLGBTQ+ ተማሪዎች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ ወደሚያደርሱ ድርጊቶችና ባህሪያት የሚመሩ የአስተሳሰብ ግድፈቶች
4. ጾታን፣ ሥርዓተ ጾታን እና የቤተሰብ ብዝሀነትን የማያካትቱ ተቋማዊ ስርዓቶችና መዋቅሮች

**ምላሽ፥**

- በDPS ውስጥ የLGBTQ+ ፕሮግራም የሥራ ድርሻ ማዘጋጀት
- ሁሉንም የቡድን አባላት መልሶ ለማደራጀት የዳታ ፕላትፎርሞችን መመዘንና ማዘመን
- ለLGBTQ+ ተማሪዎችና ቤተሰቦች እውቅና ለመስጠት Infinite Campus እና የምዝገባ ቅጾች ላይ ማሻሻያ ማድረግ
- የሥርዓተ ትምህርት ግብዓቶችን ተደራሽነት የተሳለጠ ማድረግ
- ፖሊሲዎችና አሰራሮችን የPS LGBTQ+ ቱልኪት በማዘጋጀት አማካኝነት ማቀላጠፍ
- የLGBTQ+ ማንነቶች መታየትን በDPS ማህበራዊ ትስስር ገጽ፣ የሥርዓተ ትምህርት መረጃዎች እና የማህበረሰብ ግንባታ አማካኝነት ማሳደግ
- የHR ወደ Oracle ሲስተም መሸጋገር ለሰራተኞች ሽግግር የተቀላጠፈ አሰራርን የሚይዝ ሲሆን ቢያንስ 1 ለነን ባይናሪ የሆነ ጾታ ምርጫን ያቀርባል
- በማርች 2021 ዓ.ም የደህንነት የዳሰሳ ጥናት ለተማሪዎች በDPS ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ጾታዊ መገለጫቸውን እና ጾታቸውን በማራሳቸው የሚለዩበት አማራጭ አቅርቧል። LGBTQ+ ተኮር ጥያቄዎች ተጠይቀው ነበር። የተከፋፈለ ዳታ ዲስትሪክቱን ዳታውን የLGBTQ+ ተማሪዎች ተሞክሮዎችን ለመረዳት እንዲጠቀም ያስችለዋል
- የDPS ክህሎቶች ሙያዊ ልማት ዘጋቢ በማዘጋጀት አማካኝነት ለማዕከል ተማሪ ድምጽ በመሻሻል ላይ ነው (የመጨረሻ ቀን ዲሴምበር 22 አካባቢ)።

## ማጠቃለያ

ቡድኑ ለጥሎ ማውጣትን የሚፈልጉ ሶስት ዋና ዋና ሥርዓቶችን ለይቷል። የተለዩት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስርዓቶች ሶስት ንዑስ ስርዓቶች አሏቸው። ነጥሎ ለማውጣት ተለይቶ የተቀመጠ ጠቃላላ ስርዓቶች ብዛትን ወደ አምስት
(5) ከፍ ያደርጋል። እነዚህም፥ የሚከተሉት ናቸው፥

1. የቦርድ አስተዳደር መዋቅር ወደ ፖሊሲ አስተዳደር መቀየር
2. ማዕከላዊ ጽህፈት ቤትን ከቦርዱ የመጨረሻ ፖሊሲዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ መልሶ ማደራጀት
3. ሶስት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስርዓቶች ነጥሎ ለማውጣት እንደሚያስፈልገው ተለይተዋል። እነዚህም፥
    a. የተማሪዎች ተጽእኖ ፈጣሪ ፍላጎቶች ፕሮግራም
    b. በDPS ውስጥ ለተማሪዎች ለብቻው የተዘጋጀ የትምህርት ቤት ፕሮግራም እና
    c. የክፍል 504 ፕሮግራም ልዩነት

ከላይ ተለይተው ከተገለጹት ስርዓቶች በተጨማሪ የጥቁር ልህቀት ውሳኔን እና የLGBTQ+ ኢኒሺየቲቮችን በተመለከተ በቀደሙት አያቶቻችን የተለዩ ስርዓቶችን የመለየት ስራውን ቀጥለናል።

### ተጨማሪ መርጃዎች፥

በERS ጥናት ምክረ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተ ተጨማሪ መረጃ ከዚህ ክፍል ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

ባለፈው የመኸር ወቅት ድርጅታችንን ለመገምገም እና ግብአቶችን የትምህርት ልህቀትን በሚያሻሻል መልኩ እንዴት የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም እንደምንችል ለይተን ለማወቅ በዲስትሪክት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመንግስት ፈንዶችን በማስተዳደር ሙያው ከሚታወቅ ብሄራዊ ድርጅት ከሆነው ከትምህርት ግብዓት አገልግሎቶች/ Education Resource Services (ERS) ጋር በትብብር ሰርተናል። ሙሉውን **የERS ግኝቶችን እዚህ ላይ** እንድታነቡ እንጋብዛችኋለን። እነዚህ ግኝቶች መልሶ ለማዋቀርና ጎን ለጎን ስትራቴጂያዊ እቅድ ለማዘጋጀት ለወሰድናቸው እርምጃዎች መረጃ በመስጠት አገልግለዋል። ብዙዎቹ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉትን የተከተሉ ናቸው፥

- **የDPS ውሳኔዎችና እርምጃዎች የሚመሩበትን የድርጊት ንድፈ ሀሳብ** መልሶ መመልከትና መከለስ/ማሻሻል። ለተማሪ ስኬት ይበልጥ ግልጽ የሆኑ መንገዶችን መለየት። ለአብዛኞቹ የተገለሉ ተማሪዎቻችን የሚቀርቡ እድሎችን ማስፋት። ከፍተኛ አቀበት የመውጣት ያክል ችግር ለሚገጥማቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ግብዓቶችና የተሻለ ድጋፍ ማዘዝ።
- **ለትምህርት ቤት ትስስር ማዕከላዊ ድጋፍን ማጠናከር።** በማዕከላዊ ጽ/ቤት ውስጥ ባሉ አመራሮች እና በት/ቤት ቦታዎች መሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻሻል በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ውስጥ ያለውን አንድነት ማሳደግ። በደንብ ግልጽ የሆነ መመሪያ ትምህርት ቤቶች ፈጠራ እና ቀጣይነት ያለው መሻሻል እንዲያሳዩ ያስችላቸዋል።
- **ግብዓቶች ከከፍተኛ ቅደም ተከተሎች ጋር መቀናጀታቸውን በማረጋገጥ ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ማዕከላዊ ድጋፍ ማጠናከር።** ቅደም ተከተሎቻችንን ማጠንከር። እያንዳንዱ ነገር በእኩል ደረጃ አስፈላጊ ከሆነ ምንም ቅደም ተከተሎች አይኖሩም።
- **በተማሪ ተሞክሮ ላይ እኩልነትን ለማስፈን የገንዘብ ድጋፎችን በእኩል ደረጃ ለማከፋፈል ጥረት ማድረግ።** በትምህርት ቤቶች የግብዓቶች ክፍፍል ላይ እኩልነት እንዲኖር ማድረግ (እና መቆጣጠር)።
- **የትምህርት ቤት ደረጃ የማሻሻያ እቅዶች ስለሚያመጡት መፍትሄ የሚጠበቅ ሁኔታን መወሰን እና የዲስትሪክት ደረጃ ግቦችን መደገፍ።** ይህን አቀራረብ መከተል ትብብርን ሊያሳድግ እና ቀጣይነት ያለው ስርዓት አቀፍ መሻሻልን ሊመጣ ይችላል።
- **ስራዎችን የበለጠ ጠንካራ በሆነ መልኩ ከትምህርት ቦርድ ፖሊሲ አላማዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ለማድረግ የማዕከል ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን መልሶ ማደራጀት።** ቅጽ ተግባርን መከተል አለበት።
- **የትምህርት ቤትና የማዕከል ወጪን ሆን ብሎ በቦርድ ተቀባይነት ካገኙ የዲስትሪክት ቅደም ተከተሎች ጋር ማስማማት።** በቦርድ የጸደቁ **የመጨረሻ መግለጫዎች** የትምህርት ቤትና የማእከል ድጋፍ ወጪዎች የትኩረት ነጥብ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- **በበጀት ቀመር ዝግጅትና የበጀት ትንበያ ላይ ማህበረሰቡን የበለጠ አሰራር ተኮር በሆነ መልኩ ማሳተፍ።** ይህን ማድረግ በጠንካራ ውሳኔዎች ላይ ሰፊ ግንዛቤ ለመፍጠርና ድጋፍ ለማድረግ ያስችላል።

| | | |
|---|---|---|
| | 5% | |
| TP1.2.1) የክፍል ደረጃ ጽሁፍ<br>የማንበብና መጻፍ %<br>ክፍሎች K-3 | 1.2.1k) ለሁሉም ተማሪዎች<br>የ2022 መነሻን እንደገና ማዘጋጀት<br>1.2.1l) ለጥቁር ተማሪዎች<br>አልተገለጸም<br>1.2.1m) ለላቲኔክስ ተማሪዎች<br>1.2.1n) በፕሮግራም ውስጥ ላሉ MLLs<br>1.2.1o) የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች | 60%<br>48%<br>48%<br>47%<br>28% |
| | 1.2.1p) ለሁሉም ተማሪዎች | 38% |
| TP1.2.1 | 1.2.1q) ለጥቁር ተማሪዎች | 26% |
| ማጣቀሻ % መነሻ | የ2022 መነሻን እንደገና ማዘጋጀት<br>1.2.1r) ለላቲኔክስ ተማሪዎች አልተገለጸም | 23% |
| የማንበብና መጻፍ ጉብዝና፥<br>CMAS ከ 3-8ኛ ክፍል | 1.2.1s) በፕሮግራም ውስጥ ላሉ MLLs | 13% |
| TP1.2.1 | 1.2.1t) የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች<br>7%<br>1.2.1u) ለሁሉም ተማሪዎች<br>50%<br>1.2.1w) ለላቲኔክስ ተማሪዎች<br>36% | |
| የማጣቀሻ % መነሻ ማዘጋጀት፥<br>COSAT<br>ከ 9-11ኛ ክፍል | 1.2.1v) ለጥቁር ተማሪዎች<br>41% ድጋሚ ማዘጋጀት<br>ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ማንበብና መጻፍ (EBRW)<br>1.2.1x) በፕሮግራም ውስጥ ላሉ MLLs 9%<br>1.2.1y) የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች 14%<br>አልተገለጸም<br>የ 2022 መነሻ | |

## ማጠቃለያ

ቡድኑ ለColorado Measures of Academic Success (CMAS, የኮሎራዶ የትምህርት ስኬት መለኪያዎች) ከ3-8ኛ ክፍል ሂሳብ እና ማንበብና መጻፍ፣ SAT እና ከ9-11ኛ ደክፍል PSAT አዲስ መነሻዎችን አዘጋጅቷል። ለColorado Measures of Academic Success (CMAS, የኮሎራዶ የትምህርት ስኬት መለኪያዎች) የዲስትሪክቱ ከ3-8ኛ ክፍል የሂሳብ (ተማሪዎች የሚያሳኩት ወይም ከዚያ በላይ ውጤት የሚያመጡበት) አጠቃላይ የጉብዝና/ብቃት ደረጃ 29 ነው። ከ3-8ኛ ክፍል የማንበብና መጻፍ የጉብዝና ደረጃ 38% ነው። ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የጥቁር፣ ላቲኔክስ፣ የፕሮግራም የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የCMAS የሂሳብ እና ማንበብና መጻፍ የጉብዝና ደረጃ ከዲስትሪክቱ አጠቃላይ የጉብዝና ደረጃ ያነሰ መሆኑ በታሪክ ውስጥ በተገለሉ ቡድኖች ተማሪ ላይ በCMAS ስኬት ረገድ ያሉት ስኬቶች አሁንም መቀጠላቸውን ያመለክታል።

ለCO P/SAT ከ9-11ኛ ክፍል ሂሳብ የዲስትሪክቱ አጠቃላይ ጉብዝና 31% ተማሪዎች የሂሳብ መለኪያዎችን ማሳካታቸው ወይም ከዚያ በላይ ማሳካታቸው እና በማንበብና መጻፍ 38% ተማሪዎች ማሳካታቸው ነበር። ከCMAS ጋር በተመሳሳይ በተማሪ ቡድኖች መካከል ያሉት ክፍተቶች ቀጥለዋል። ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው በቆዳ ቀለም በተለዩ ተማሪዎች፣ የMLL ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ላይ በንባብ እና ማስረጃ ተኮር ማንበብ እና ጽሁፍ ላይ አለመመጣጠኖች ይታያሉ።

ከK-3ኛ ክፍል የተካሄዱ የቅድመ ማንበብና ጽሁፍ የREAD Act ምዘናዎችን በተመለከተ ከላይ ሰንጠረዡ የ2022 ዓ.ም መነሻ ለሁሉም ተማሪዎች 60% እንደሆነ አስቀምጧል። ጥቁር ተማሪዎች፣ ላቲኔክስ ተማሪዎች፣ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ወይም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከሌሎች ደረጃዎች ያነሱ የጉብዝና ደረጃዎችን አግኝተዋል።

የ2021-22 ዓ.ም የትምህርት ዓመት ትኩረታችን የወደፊት የትምህርት ዓመታት መነሻን ማዘጋጀት ነበር። ጥቁር፣ ላቲኔክስ፣ የአገሬው ተወላጅ አሜሪካውያን፣ MLLs፣ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና ሌሎች ተማሪዎቻችን እድገት የሚያመጡባቸውን መስመሮች በማፋጠን መነሻችንን መሰረት ማስያዝና ውጤቶቹን ማሻሻል ላይ ትኩረት አድርገን ነበር። ስትራቴጂያዊ ፍኖተ ካርታ ሁሉንም እነዚህን ሚዛን ውስጥ በማስገባት አላማ ተኮር በሆነ መልኩ እንደተዘጋጀ እና በተማሪዎች መካከል የቀጠሉትን የትምህርት አፈጻጸም ልዩነት እና ክፍተቶች ለመፍታት በጥሩ ሁኔታ እንደሚያገለግል አምናለሁ። ቡድኔ እና እኔ የማንበብና መጻፍ ጉብዝና ከሂሳብ በላይ የተመለከትን በመሆኑ ይህን በትምህርት ቤቶቻችን የመመሪያ አሰጣጥ አዝቅድ ዝግጅት ለመፍታት እንሰራለን።

ለDPS በሁሉም ትምህርት ቤቶቻችን የሁሉም ተማሪዎቻችንን የተፋጠነ የእድገት መስመር ለማሳካት 1) በምቹና ጋባዥ የትምህርት መቼቶች፣ እና 2) በክፍል ደረጃ ጽፎችና ተግባሮች ወሳኝ አስፈላጊነት ላይ አጽንኦት መስጠት እፈልጋለሁ። ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ልክ ወይም ከዚያ በላይ አፈጻጸም እንዲኖራቸው የክፍል ደረጃ ትምህርቶችን/ስራን አዘጋጅቶ በምቹና ጋባዥ የትምህርት መቼቶች መስጠት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ። የትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት ትምህርት ቤቶችን በእነዚህ ሁለት መሰረቶች ላይ እጅግ አጥብቦ ላማጣመርና ትኩረት ለማድረግ ለትምህርት ቤቶች ትምህርት፣ የትምህርት ቤት ቁጥጥርና በትምህርት ቤቶች ድጋፍ መምሪያዎች በኩል ድጋፍ እያደረገ ነው።

የበለጠ ዘርዝር ባለ ደረጃ ዲስትሪክቱ በማንበብና መጻፍ፣ በሒሳብ እና የሙሉ ህጻናት አቀራረብን በሚደግፉ በሌሎች የይዘት መስኮች መካከል ምጣኔ መፈለግ ያስፈልገዋል። በተለይም በሂሳብ ላይ መሰራት ያለባቸው በርካታ ስራዎች አሉ። ተግባሮችን በመተግበር፣ ተማሪዎችን ውጤታማ ለመሆን እንዲታገሉ ግፊት በማድረግ እና መምህራንን ለተማሪዎቻቸው በዚሁ መልኩ ድጋፍ እንዲያደርጉ እውቀታቸውን፣ ክህሎቶቻቸውን እና የአእምሮ ዝግጁነታቸውን በማሳደግ ጽናታችን ለመቀጠል ትኩረት መስጠት አለብን። ዲስትሪክቱ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚያደርገውን ግልጽ የቋንቋ መመሪያ አሰጣጥና የቋንቋ ድጋፍ እንደገና ማዘጋጀት አለበት። ይህ አቀራረብ MLLsን የበለጠ ትርጉም ባለው መልኩ ይደግፋል እንዲሁም ሁሉንም ተማሪዎች ተጠቃሚ ያደርጋል።

የCMAS፣ COSAT፣ እና READ Act ዳታችን የሚገኝበት ደረጃ ዲስትሪክቱ እንዲገኝ በሚፈልግበት ደረጃ ላይ አለመገኘቱን እና ዲስትሪክቱ በተገለሉ የተማሪ ቡድኖች መካከል የታዩ አጠቃላይ የአፈጻጸም ደረጃዎች ልዩነትን እና ክፍተቶችን ለመፍታት እየሰራ እንደሚገኝ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ዳታው የሚያስደንቅ አይደለም። በወረርሽኙ ወቅት የነበረው የተማሪ አፈጻጸም በሚፈለገው ደረጃ ያልነበረ መሆኑና የወረርሽ መከሰት ሁኔታውን ያባባሰው መሆኑ ግልጽ ነው። ስትራቴጂያዊ ፍኖተ ካርታው በመደበኛ ምዘናዎች ላይ ያለውን ዝቅተኛ አፈጻጸም ለመፍታት የሚያስችል ጥቅም እንደሚያስገኝልን እርግጠኛ ነን።

## RI.3 - የተማሪና ሰራተኛ ደህንነት

**ለ21/22 ይህን የመጨረሻ መግለጫ ማሟላት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሳካል፥**

1. 85% ትምህርት ቤቶች ግልጽ የSEL ስርዓተ ትምህርት ሲኖራቸው።
2. ዲስትሪክቱ መነሻ ሲዘጋጅ እና ለሁሉንም ከመኸር ወቅት የተወሰዱትን የBESS የተማሪና መምህር ማጣሪያዎች የሚያደርግ ከሆነ። ይህ ምዘና በዓመት ሶስት ጊዜ በትምህርት ቤቶች ይተዳደራል።
3. ከ0-10 መለኪያ ደህንነትን 7 ወይም ከዚያ በላይ አድርገው ሪፖርት ያደረጉ ሰራተኞች % ከመኸር ወቅት እስከ ፀደይ ወቅት ድረስ ጨምሯል።
4. እያንዳንዱ የማህበረሰብ ማዕከል ተማሪዎችን በደህንነታቸው ላይ ለመደገፍ ታስበው የተዘጋጁ የአገልግሎት ማውጫዎች ያሏቸው ሲሆን ተማሪዎች አገልግሎቶቹ ፍላጎቶቻቸውን እንዳሟሉላቸው ሪፖርት ያደርጋሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.3.2 በመኸር ወቅት ከነበረው ከፍተኛ በፀደይ ወቅት ወደሚኖረው **መደበኛ የሚቀየሩ የBESS የተማሪና መምህር ማጣሪያዎች መነሻ % ማዘጋጀት** | አጠቃላይ | አይመለከተውም<br>አይመለከተውም<br>ቦታ<br>አይመለከተውም<br>የ 22 መነሻ<br>አይመለከተውም<br>አይመለከተውም | 45.0% |
| | ለጥቁር ተማሪዎች | | 42.9% |
| | ለላቲኔክስ/ሂስፓኒክ ተማሪዎች | | 46.2% |
| | የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች | | 50.0% |
| | በፕሮግራም ውስጥ ላሉ የ MLL ተማሪዎች | | 46.1% |
| | | **ጃንዋሪ 2022** | **ሜይ 2022** |
| | 1.3.3a) ለሁሉም ሰራተኞች | 6.4 6.2 | 6.2 |
| 1.3.3) የሚሰጡት ሃሳብ/Tu Voz | 1.3.3b) ለBIPOC ሰራተኞች | 5.6 5.4 | 6.7 |
| ከ0 እስከ 10 መለኪያ አማካኝ | 1.3.3c) በራስ ለሚለይ | LGBTQ+ ሰራተኞች<br>1.3.3d) መምህራን<br>1.3.3e) ለትምህርት ቤት መሪ | 6.2 6.0 6.2<br>6.0 5.8 6.0<br>5.5 5.3<br>6.3 |

### ማጠቃለያ

ይህ ዓመት ዲስትሪክቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ተመልሰው ወደ መማሪያ ክፍልና ወደ ትምህርት ቤት ህንጻዎች በተመለሱበት ወቅት ተጨማሪ የአእምሮ፣ የአካልና የሥነ ልቡና ድጋፍ ማግኘት የፈለጉበት ዓመት እንደሆነ የተገነዘበበት ነው። ሁሉም ትምህርት ቤቶቻችን በቀን ቢያንስ ለ20 ደቂቃዎች በSEL ትምህርት ላይ እንዲሳተፉ እና ይህን ትምህርት በመሪ እቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱ የተጠየቁት በዚህ ምክንያት ነበር። በBESS የዳሰሳ ጥናት የተሰበሰበው መነሻ ዳታ ለዲስትሪክቱ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች ደረጃ ጥልቅ ሀሳቦችን የሰጠው ከመሆኑም በተጨማሪ ለተማሪ ፍላጎት ፈጣን ምላሽ ስለሚሰጥበት ሥርዓተ ትምህርት እና/ወይም ስትራቴጂዎች የተሻለ ግንዛቤ ፈጥሮለታል።

ይህ የመነሻ ዳታ በተጨማሪም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ባህል ለመገንባት በሚደረጉት ጥረቶችና ኢኒሺየቲቮች ላይ ትምህርት ቤቱን እንድንደግፍ እና በእነዚህ ጥረቶች ላይ ተመስርተን የትኞቹ የተማሪ ቡድኖች ተጨማሪ ድጋፎች እንደሚያስፈልጓቸው በግልጽ እንድንረዳ አስችሎናል።

የከፍተኛ አመራር ቡድኑ ለBESS የተማሪና መምህር ማጣሪያዎች በመኸር ወቅት 2021 ከነበረበት "የከፍተኛ" ምድብ በጸደይ ወቅት 2022 ወደ "መደበኛ" ምድብ የሚቀየር መነሻ መነሻ % አዘጋጅቷል። ይህ የመነሻ ዳታ በአጠቃላይ ልንጠብቅ እንደምንችለው 45% ተማሪዎቻችን በመኸር ወቅት ከነበረው የከፍተኛ ምድብ በፀደይ ወቅት ወደሚኖረው መደበኛ ምድብ እንደሚጋገሩ ያመለክታል። በተጨማሪም ቡድኑ በ"የእርስዎ ድምጽ/TuVoz" ዳሰሳ ጥናት ላይ ተመስርቶ ከመኸር ወቅት እስከ ፀደይ ወቅት ጨምሮ እንደታየው ከ0-10 መለኪያ ለደህንነት 7 ወይም ከዚያ በላይ ውጤት በመስጠት ሪፖርት የሚያደርጉ ሰራተኞች % አዎንታዊ ሂደት አዘጋጅቷል። በቅርቡ የተካሄደው መልሶ ማደራጀት በዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች ላይ ተጽእኖ እንደፈጠረና ይህም የ"ሁሉም" ሰራተኞች አማካኝ ውጤት ከመኸር ወቅት እስከ ፀደይ ወቅት ድረስ ተመሳሳይ ሆኖ እንዲቀጥል እንዳደረገ እስባለሁ።

**በአጠቃላይ ሁሉም የመቆጣጠሪያ ሪፖርት አቀራረብ መለኪያዎች ተሟልተዋል።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.3.1a) ለSEL የተለየ ሥርዓተ ትምህርት ያላቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት | በዲስትሪክት የሚመራ | 85% 33% | 100% |

**አንድ መቶ ፐርሰንት በዲስትሪክቱ የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች በ2022-23 UIPs ውስጥ የSEL ስርዓተ ትምህርት ለይተው ማስቀመጣቸው ይህ ዒላማ ከተፈላጊው በላይ እንዲሳካ አድርጓል።** የዲስትሪክቱ የTSEAL ቡድን ለሁሉም ትምህርት ቤቶች የዕለታዊ ግልጽ የመመሪ አሰጣጦች ግብአቶችን እያቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ ዲስትሪክቱ እንደ Harmony for elementary schools and Second Step፣ Facing History ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እና Power Collaborative ለመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመሳሰሉ ከሥርዓተ ትምህርት የተገኙ ግብአቶችን እያደለ ነው። ትምህርት ቤቶች የተለዩ ግብዓቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ ይህን በUIPያቸው ውስጥ ለይተው ማመልከት አለባቸው። የTSEAL አሰልጣኞች በተጨማሪም ለትምህርት ቤቶች የአሁኖችን ሥርዓተ ትምህርቶች የሚቀሙ ከሆነ በስርዓተ ትምህርት ትግበራ ላይ ድጋፍ ያደርጉላቸውል።

## RI.4 - ጤናና ደህንነት

**ለ21-22 ይህን የመጨረሻ መግለጫ ማሟላት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሳካል፥**

1. ዲስትሪክቱ የDenver Department of Public Health &Environment (DDPHE, ዴንቨር የማህበረሰብ ጤናና አካባቢ መምሪያ) የክትባት ኃላፊነቶችን 100% ሲያሟላ።
2. ዲስትሪክቱ የወረርሽኙን ስርጭት ለማቅለል ለተማሪዎችና አዋቂዎች የሚቀርቡት የክትባት መጠኖች ከCDPHE እና CDC መመሪያዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ
3. ዲስትሪክቱ በተማሪዎች ላይ ለሚጥላቸው ከትምህርት ቤት ውጭ የመቆት እገዳዎች ብዛት ቁጥራቸውን በተማሪ የሥነ ምግባር ቡድን (የጁን 2022 የቁጥር ሪፖርት) በሚመዘነው መሰረት ከ2018-19 መርሀ ግብሮች እንዳይበልጥ አድርጎ መነሻ ሲያዘጋጅ
4. ዲስትሪክቱ ወቅታዊ የጤና ሁኔታዎቻችን በሚፈቅዱት መሰረት የገጽ ለገጽ ትምህርት ቤት ተደራሽነት ቅድሚያ ተሰጥቶት የሚቀጥል መሆኑን ሲረጋግጥ።
5. ዲስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ድጋፎች የመሳሰሉ ግብዓቶችን ሲጠቀም። (ለትምህርት ቤቶች የማእከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች መመደብ፣ የንግድና የማህበረሰብ አጋሮችን እንደ ድጋፍ ምንጭ መጠቀም፣ ወዘተ)

<table>
<tr>
<td>1. የCOVID ተጽእናዎች በተማሪዎቻችን የመማሪያ ቦታዎችም ይሁን በሰራተኞች የስራ ቦታዎች ላይ የቀነሱ ከመሆኑም ባለፈ የDDPHEን የክትባት ኃላፊነት 100% ለማሟት ከአካባቢና የግዛት የጤና ባለስልጣናት ጋር የቅርብ ትብብር በማድረግ እንሰራለን፤ ከበሽታው ስርጭት ይልቅ የተቆጣጣሪ ሰራተኞች የመከተብ መጠኖች በCDPHE በእጅጉ የሚመከር ከመሆኑም ባለፈ DPS ሊቆጣጠር ከሚችለው ነገር ጋር የተጣጣመ ነው።</td>
<td colspan="2">የ Denver ከተማና ካውንቲ በኦገስት 2021 ዓ.ም ክትባቶች መውሰድን የሚጠይቅ የማህበረሰብ ጤና ትእዛዝ አውጥቶ ነበር። እስከ ኖቬምበር 2021 ዓ.ም ድረስ ይህ 97.6% ተሟልቷል። ሌሎች 2.4% ሰራተኞች ዓላማውን ትእዛዝን እንዲከብሩ ማድረግ የሆነ እያደገ የሚሄድ የሥነ ምግባር እርምጃ ተወስዶባቸዋል። የHR ቡድኖች ሰራተኞቹን የታዘዟቸውን ትእዛዞች ወይም አገልግሎቶች እንዲያጠናቅቁ እንደ የኢንተርኔት ተደራሽነት ወይም ቴክኖሎጂ የመሳሰሉ ግብዓቶችን ተደራሽ አድርገው ነበር። በገጽ ለገጽ ዝግጅቶች ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስፓኒሽ የሆኑ ተናጋሪዎችን የሚደግፉ ተርጓሚዎች ተመድበው ነበር። የቡድን አባላት ለትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ካልሆኑ ሰራተኞች ላይ ሰነዶችን ለመሰብሰብ ወደ ብዙ የተለያዩ ቦታዎች ተጉዘው ነበር።</td>
<td>ዲስትሪክቱ በጠቅላላው 15,418 ክትባቶችን በማቅረብ ለ8,874 ሰራተኞችና ተማሪዎች ግልጋሎቶችን ሰጥቷል። ክትባቶቹ የተሰጡት በ17 ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የጤና ክሊኒኮች፣ 11 አጠቃላይ ክሊኒኮች እና 10 የDPS ትምህርት ቤቶች ነበር።<br><br>ከጃንዋሪ 2022 ዓ.ም ጀምሮ የDPS የተማሪ የክትባት መጠን 43% ሙሉ በሙሉ እና 7.7% በከፊል ተጠናቋል።<br><br>እኛ የDPS ሰራተኞች እንደመሆናችን የማህበረሰብ ጤና ትእዛዝ (PHO) ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የDenver ከተማና ካውንቲን የክትባት ኃላፊነቶች እናከብራለን። በአሁኑ ወቅት ምንም PHO እና HR የሌለ በመሆኑ ስለ ወደፊት አጋዥ ክትባቶች ወይም አዲስ ክትባቶች በተመለከተ የCOVID ክትባት መረጃ መሰብሰብ አያስፈልግም። አዲስ የPHO ኃላፊነት የሚወጣ ከሆነ ለዚህም ታዛዥ እንሆናለን።</td>
</tr>
<tr>
<td>2.የCOVID ተጽእኖዎች በተማሪዎቻችን የመማሪያ ቦታዎችም ይሁን በአስተማሪና በሰራተኞች የስራ ቦታዎች ላይ የቀነሱ ከመሆኑም ባለፈ ከአካባቢችን እና የግዛት የጤና ባለስልጣናት ጋር የቅርብ ትብብር በማድረግ እንሰራለን</td>
<td>የተማሪዎች የክትባት መጠኖች ላይ ቁጥጥር እናደርጋለን</td>
<td>ከበሽታው ስርጭት ይልቅ የተማሪዎች የመከተብ መጠኖች በCDPHE በእጅጉ የሚመከር ከመሆኑም ባለፈ DPS ሊቆጣጠር ከሚችለው ነገር ጋር የተጣጣመ ነው።</td>
<td>በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ወረርሽኝ በተከሰተባቸው ጊዜያት ትምህርት ቤቶችን ክፍት ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ እንደ የፊት ጭምብል መልበስ እና ወደ ውስጥ የሚገባውን የአየር መጠን መጨመር ያሉ ተጨማሪ የDDPHE ምክረ ሀሳቦችን ተግባራዊ አድርገናል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ምንም ተጨማሪ ምርመራዊች ያልተሰጡ ቢሆንም፣ Omicron በብዛት የተስፋፋ ጊዜ፣ በተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ምልክቶች የሚታዩ ከሆነ ከሰራተኞች ጋር ወደቤት ልከን ለተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ልንሰጥ የምንችላቸው ከበቂ በላይ</td>
</tr>
</table>

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | መጠባበቂያ በቤት ውስጥ የሚሰጡ የCOVID ፈጣን ምርመራዎች ነበሩን። <br><br> የዲስትሪክታችን የነርሲንግ ዳይሬክተር በማህበረሰብና የትምህርት ቤት የCOVID ተያዥ ጉዳዮች ላይ ቁጥጥር ማድረጉን የሚቀጥል ከመሆኑም በተጨማሪ የCOVID መንሰራፋት መጠኖች ለመቆጠር ከDDPHE ወረርሽኝ ተቆጣሪ ቡድን ጋር ሳምንታዊ ስብሰባ ያካሂዳል። የማቅለያ ስትራቴጂዎች የታወቀ የወረርሽኝ ስርጭት ደረጃ ላላቸው ትምህርት ቤቶች የሚመከሩ እንደመሆኑ እነዚህን ምክረ ሀሳቦች እንደ አስፈላጊነቱ ለቤተሰቦቻችን ማሳወቃችንን እንቀጥላለን። |
| 4. የተማሪ ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ | የጤና ሁኔታዎቻችን በሚፈቅዱበት ጊዜ የገጽ ለገጽ ትምህርት ተደራሽነት ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደሚቀጥል እናረጋግጣለን | በአሜሪካ የህጻናት ሀኪሞች አካዳሚ (American Academy of Pediatrics) የተካሄደ የምርምር ጥናት የገጽ ለገጽ ትምህርት አብዛኞቹን ከCOVID-19 ወረርሽኝ ጋር ተያያዥ የአእምሮ ጤና ተግዳሮቶችን ለማቅለል እጅግ ውጤታማ ዘዴ እንደሆነ አሳይተዋል። <br><br> https://www.aap.org/en/pages/2019-novel-coronavirus-covid-19-infections/clinic <br><br> al-guidance/covid-19-planning-considerations-return-to-in-person-education-in-schools/ | በ21/22 ዓ.ም የትምህርት ዓመት ውስጥ የትምህርት ቤት ቡድኑ ከተግባር ሙያተኞች ቡድናችን ጋር በትብብር ትምህርት ቤቶች በጊዜያዊነት ወደ ቨርቹዋል ትምህርት ለማለፍ የሚጠይቁበትን አሰራር አዘጋጅቷል። <br><br> ይህ ፕሮቶኮል በመጨረሻ እንዲፀድቅ በበላይ ተቆጣጣሪው ጠረጴዛ ላይ ከቀረቡ ጥያቄዎች ጋር በርካታ የማጣራት እርከኖችን የሚያልፍበትን ፕሮቶኮል ፈጥሯል። <br><br> ለትምህርት ቤቶች ወደ ቨርቹዋል ትምህርት እንዲቀየሩ ከመፈቀዱ በፊት ትምህርት ቤቶች የገጽ ለገጽ ትምህርትን ለማስቀጠል እያንዳንዱን አስፈላጊ እርምጃን መውሰዳቸውን እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ። |
| 5. የገጽ ለገጽ ትምህርት ተማሪዎችን ብዛት ማሳደግ | ትምህርት ቤቶችን ከፍት እንደሆኑ ለማስቀጠል ሌሎች የድጋፍ ምንጮችን ይጠቀማል። (ለትምህርት ቤቶች የማእከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች መመደብ፣ የንግድና የማህበረሰብ አጋሮችን እንደ ድጋፍ | የጤና ቀውሶች የሚያጋጥሙ ከሆነ ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው እንዲቀጥሉ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የሰራተኛ ምደባ ምንጭ ጥቅም ላይ ይውላል | በ2021-22 ዓ.ም የትምህርት ዓመት ውስጥ በሙሉ ብዙ ጊዜያት የCOVID ወረርሽኝ ከፍተኛ የሰራተኛ ምደባ ጉዳዮችን ፈጥሮ ነበር። የገጽ ለገጽ ትምህርቱን ለማስቀጠል እንዲቻል Dr. Marrero የትምህርት ቤቶች የሥራ ድርሻዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመሸፈን ብቁ የሆኑ የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞችን ዝርዝር ለማዘጋጀት ከኤችአር እና የትምህርት ቤቶች ቡድን ጋር አብረው ሰርተዋል። |

| | | |
|---|---|---|
| | ምንጭ መጠቀም፣ ወዘተ) | የማስማራት ጥረቱ ከ1190 የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች መካከል 640 ሰራተኞችን ያካተተ ሲሆን በብዙዎቹ ትምህርት ቤቶቻችን እስከ ትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ቀጥሎ የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ የገጽ ለገጽ ትምህርትን ማስቀጠል አስችሎናል። ይህ ሊሳካ የቻለው ትምህርት ቤቶችን ወጥነት ባለው መልኩ እንዲቀጥሉ በሚያስችሉ የቋሚ ሽፋን ምደባዎች በውጥረት ጊዜያት ሁሉ የሚደረገውን ድጋፍ ማድረግ በማስቀጠል ነበር። ትምህርት ቤቶች በማይገኙ ሰራተኞችና በሚያገለግሏቸው ተማሪዎች ብዛት ብዛት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ተብለው ተለይተው ነበር። በጠቅላላው 43 ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ትምህርት ቤቶች ተለይተው ፍላጎቱን ለማሟላት አራት (4) የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች ሰኞ፣ ማክሰኞ እና አርብ እንዲሰሩ ተመድበው ነበር። ፍቃድ የተሰጣቸው የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች ከፍተኛ ፍላጎት ላላቸው ትምህርት ቤቶች ቅድሚያ ይሰጣቸው ነበር።<br><br>HR ተተኪዎችን ለመሳብ እና ይዘን ለመቀጠል እንድንችል ለመርዳት የተተኪዎችን የሰዓት ክፍያ ለማሳደግ ከመስራቱም በተጨማሪ የተጋባዥ መምህር የፍቃድ ክፍያዎችን ከፍሏል። ከዚህ በተጨማሪም በወር በሚሰጡ የስራ ምደባዎች ላይ ተመስርተን የጥሬ ገንዘብ ማበረታቻዎችን ሰጥተናል። ይህ የመማሪ ክፍሎች ባዶ እንዳይሆኑ የመሸፈን አቅማችን እንዲያድግ በማድረግ ረድቶናል። |

| | | |
|---|---|---|
| TP 1.4.3<br>በአንድ መቶ ተማሪዎች የሚጣሉ ከትምህርት ቤቶች እገዳዎች (OSS) መነሻን እንደገና ማዘጋጀት እና እነዚህ ከ2018-19 መጠን እንዳይበልጡ ማድረግ | 1.4.3a) አጠቃላይ 4.25 ወይም ከ4.25 በታች | 4.14 |
| | 1.4.3b) ላቲኔክስ 4.04 ወይም ከ4.04 በታች | 4.21 |
| | 1.4.3c) MLL 3.98 ወይም ከ3.98 በታች | 3.75 |
| | 1.4.3d) አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች 10.81 ወይም ከ10.81 በታች | 10.30 |
| | 1.4.3e) ጥቁር ተማሪዎች 10.15 ወይም ከ10.15 በታች | 9.16 |
| | 1.4.3f) ጥቁር ሴት 8.08 ወይም ከ8.08 በታች | 8.15 |
| | 1.4.3g) ጥቁር ወንድ 13.27 ወይም ከ13.27 በታች | 10.16 |

TP1.4.5
የDPS አማካኝ የደህንነት ምላሽ ብዛቶች (ከጁላይ ‘21-ጁን ‘22

TP1.4.3a) ቅድሚያ 1 5 ደቂቃዎች 7 ደቂቃዎች 4 ደቂቃዎች TP1.4.3b) ቅድሚያ 2 12 ደቂቃዎች 15 ደቂቃዎች 12 ደቂቃዎች TP1.4.3c) ቅድሚያ

3 12 ደቂቃዎች 15 ደቂቃዎች 12 ደቂቃዎች

## ማጠቃለያ

ከፍተኛ አመራሩ በመቶ ተማሪዎች ለሚጣሉ ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳዎች (OSS) መነሻ አዘጋጅቷል። ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው ከ4.04 እስከ 4.21 እና ከ8.08 እስከ 8.15 በመቶ ተማሪዎች በቅደም ተከተል 4.2% እና 9% ጭማሪ ካሳዩት የላቲኔክስ ተማሪዎች እና የጥቁር ሴት ተማሪዎች እገዳዎች በስተቀር ይህ አጠቃላይ ኢላማ ለእያንዳንዱ ምድም ከተቀመጡት ኢላማዎች ጋር ተሳክቷል። ዲስትሪክቱ በተጨማሪም የእነዚህን ጭማሪዎች ስረ መሰረቶች መርምሮ በሌሎች ምድቦች ስር የተቀመጡትን ኢላማዎች ከማሰካት ጎን ለጎን ወደፊት በላቲኔክስና ጥቁር ሴት ተማሪዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን ይቀምራል። ተጨማሪ ሊደነቅ የሚገባው ነጥብ የጥቁር ተማሪዎች አጠቃላይ OSS 9.75% መቀነሱ ነው። ይህን ስኬት በከፊል ለጥቁር ልህቀት እቅዶች ከሰጠሁት ትኩረት አገናኘዋለሁ።

የDPS የደህንነትና ፀጥታ ቡድን የምላሽ መስጫ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና የቅድሚያ 1፣ 2 እና 3 ኩነቶች ኢላማዎችን በማዘጋጀት ረገድ ስኬታማ ነበር። ለ2022/23 SY ቡድኑ ለቅድሚያ 1 በ7 ደቂቃዎች አማካኝ ጊዜ ምላሽ በመስጠት እና ለቅደም ተከተል 2 እና 3 ከ15 ደቂቃዎች ባነሰ ጊዜ ምላሽ በመስጠት ስኬታማ ነበር።

**በአጠቃላይ ከላቲኔክስና ጥቁር ሴቶች ምድቦች በ100 ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳዎች በስተቀር ሁሉም ኢላማዎች ተሳክተዋል። ስለሆነም በዚህ የግምገማ ጊዜ ውስጥ ከ10 ኢላማዎች መካከል 8ቱ ተሳክተዋል።**

# RI.5 - ድህረ ምርቃትና አጠቃላይ ዜግነት

**ለ21/22 ይህን የመጨረሻ መግለጫ ማሟላት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሳካል፥**

1. ዲስትሪክቱ በወረርሽኙ ምክንያት የ4 ዓመት፣ የ5 ዓመት፣ የ6 ዓመት እና የ7 ዓመት የተመራቂ መጠን መነሻዎችን እንደገና ያዘጋጃል። የተመራቂ መጠን ዳታ የሚሰላው በCDE ነው። ወረርሽኙ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመራቂዎች እና ተምህርት የሚያቋርጡ መጠኖች ላይ የፈጠራቸው ተጽእኖዎች እስካሁን በብሔራዊ ዳታ ሂደቶች ያልተገለጹ በመሆኑ ይህን ማድረጉ አሳማኝ ነው።
2. ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተመራቂዎች መጠንን ለማሳደግ በትክክለኛው የመመረቂያ መስመር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መነሻ ማዘጋጀት። በColorado ግዛት የመመረቂያ መስፈርቶች መሰረት ተማሪዎች ለመመረቅ የብቃት ደረጃቸውን ማሳየት የሚገባቸው በመሆኑ ምክንያት ይህን ማድረጉ ተገቢ ነው።
3. በወረርሽኙ ምክንያት ከተፈጠረው መስተጓጎል በSeal of Biliteracy ለሚመረቁ ተማሪዎች መነሻ እንደገና ማዘጋጀት።
4. ሁሉም በዲስትሪክቱ የሚመሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፋይናንስ እውቀት ትምህርቶችን ይሰጣሉ። ይህ ዲስትሪክቱ በ22/23 ዓ.ም የትምህርት ዓመት 100% የትምህርት ቤቶቹን ህንጻዎች በመገንባቱ ይረጋገጣል።

| | | |
|---|---|---|
| | | |
| TP1.5.7 # በSeal of Biliteracy የሚመረቁ ተማሪዎች # (ሊሰራ የሚችል ንዑስ መለኪያ- ከስፓኒሽ ውጭ የሌሎች ቋንቋዎች %) (ክብደት=1) | በዲስትሪክት የሚመራ አልተገለጸም የ2022 መነሻን እንደገና ማዘጋጀት | <u>ይህን መለኪያ ሪፖርት ማድረጉ በSeal of Biliteracy ተመራቂዎች ላይ ዳታ ባለመገኘቱ ምክንያት በSLT ጥያቄ ወደ አገስት ተዛውሯል።</u> |
| | | የ 2021 ተመራቂዎች |
| | 1.5.1a) ለሁሉም ተማሪዎች | 74.0% |
| TP1.5.1a በወረርሽኙ ወቅት ለነበሩት የክፍል ደረጃ መጠኖች መለኪያ ማዘጋጀት | 1.2.1b) ለጥቁር ተማሪዎች (4-ዓመት)<br>1.2.1c) ለላቲኔክስ ተማሪዎች (4-ዓመት)<br>1.2.1d) በፕሮግራም ውስጥ ላሉ MLLs (4 ዓመት)<br>1.2.1e) የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች (4 ዓመት) — አልተገለጸም — በ2022 ውስጥ መነሻውን ማዘጋጀት<br>1.2.1f) የ5-ዓመት የክፍል ደረጃ መጠን<br>1.2.1g) የ6-ዓመት የክፍል ደረጃ መጠን<br>1.2.1h) የ7-ዓመት የክፍል ደረጃ መጠን | 71.7%<br>69.5%<br>52.7%<br>55.1%<br>80.3%<br>79.4%<br>79.4% |

## ማጠቃለያ

የጥቁር እና ላቲኔክስ ተመራቂዎች መጠን ከ2018-19 ዓ.ም ደረጃዎች የበለጠ ቢሆንም በMLL እና SWD ተማሪዎች ብዛት ላይ መቀነስ ተስተውሏል። ይህ በወረርሽኙ ምክንያት በተለይም በSPED ውስጥ ካጋጠሙት የሰራተኞች እጥረቶች ጋር ተያዥነት ካላቸው የተለያዩ ምክንያቶች ጋር ሊገናኝ ይችላል። በአገር አቀፍ ደረጃ የSPED መምህራን እጥረት ማጋጠሙ በተማሪ የመመሪያ አሰጣጥና በጥቅላላው በSPED የIEPs መሟላት ላይ ያሉትን ክፍተቶች እንዲሁም ምክረ ሀሳቦች በዐቢይ መምህራን እና የSPED መምህራን በተሟላ ሁኔታ በሚተገበሩበትና ግንዛቤ በሚወሰድበት ሁኔታ የተማሪን ለከፍተኛ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ተደራሽነት ለማሻሻል በታሰቡ ጣልቃገብነቶች ላይ ያላውን ክፍተት አባብሶታል። በአገር አቀፍ ደረጃ ያጋጠመው የSPED ሙያተኞች እጥረት በተጨማሪም በመምህራን ላይ ያለውን የሥራ ጫና ከፍ አድርጎታል።

ዲስትሪክቱ ተማሪዎቻችን ወደ ድህረ ወረርሽኝ የትምህርት ክፍል ሲመለሱ ከሚያስፈልጓቸው ነገሮች ጋር አጣጥሞ ሁሉንም የSPED መምህናንን፣ ለመቅጠር፣ ይዞ ለመቀጠል እና መልሶ ለማሰልጠን በንቃት እየሰራ ነው። ዲስትሪክቱ IEPs በትክክል መጻፋቸውንና መተግበራቸውን በሚያረጋግጡ የስልጠናና ተጠያቂነት ስርዓቶች እንዲሁም ለክፍል ደረጃ ይዘት ተደራሽነት ድጋፍ ወጥነት ያለው ትግበራ በሚያገለግሉ ተመራጭ አሰራሮች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ከSPED በተጨማሪ ዲስትሪክቱ ቅልቅል ሞዴል ለተማሪዎች መመሪያ አሰጣጥ እጅግ ውጤታማ ሞዴል አለመሆኑን በሚያመለክት መልኩ የMLE የተማሪ ዳታ መውረድ እንዳለ ተገንዝቧል። ዲስትሪክቱ በአሁኑ ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች ግልጽ የቋንቋ መመሪያ (ELI) አሰጣጥን የሚደግፍ፣ በMLE ፍላጎቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግና ተማሪዎቹ የትምህርት ይዘቱን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲወስዱ የሚደግፍ እና ጥብቅ የክፍል ውስጥ መመሪያ አሰጣጥን ስራ ላይ የሚያውል የማስተማር-መማር ሳይክል ለመተግበር እየሰራ ነው። የፍትህ መተግበርን ለማወቅ እንደ አንድ ክፍል ተማሪዎች በእጅጉ አሳታፊ የሆኑ ለባህል አግባብነት ያላቸውና በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ የትምህርት መርጃዎችን እያገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በስርዓተ ትምህርቱ ላይ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህ ስራ ቀጣይነት ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ በቀጣይ በተመራቂ ተማሪዎች መጠን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይፈጥራል።

**ባጠቃላይ ዲስትሪክቱ ለሁሉም ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ለተለዩት ምድቦች መነሻ አዘጋጅቷል።** ይህ መነሻ ዲስትሪክቱን ለወደፊት የተመራቂዎች መጠኖች አሳማኝ ኢላማዎችን እንዲወስን ያስችለዋል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| TP1.5.2 ለአዲስ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በትክክለኛው የመመረቂያ መንገድ (OTG) ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መነሻ ማዘጋጀት (AYG 2023) | | የ2022 መነሻን እንደገና ማዘጋጀት<br>**ክሬዲት** | **የብቃት /COMPETENCY/ መስፈርት** |
| | 1.5.2a) ለሁሉም ተማሪዎች | 65% | 54% |
| | 1.5.2b) ለጥቁር ተማሪዎች | 60% | 41% |
| | 1.5.2c) ለላቲኔክስ ተማሪዎች አልተገለጸም | 58% | 44% |
| | 1.5.2d) በፕሮግራም ውስጥ ላሉ MLLs | 38% | 14% |
| | 1.5.2e) የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች | 44% | 17% |
| TP1.5.7 Seal of Biliteracy የሚመረቁ ተማሪዎች # | ለሁሉም ተማሪዎች አልተገለፀም (ከስፓኒሽ በስተቀር የሌሎች ቋንቋዎች ሊሰራ የሚችል መለኪያ %) | የ2022 መነሻን እንደገና ማዘጋጀት<br>845 ተማሪዎች (በቋንቋ ከ45 ትምህርት ቤቶች የተረጋገጠ)<br>(798 ተማሪዎች በይደር ተይዘዋል)<br>**ይህ ሁሉም የምዘና ውጤቶች እስከሚቀርቡ ድረስ አይቀርብም** | |
| TP1.5.8 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለፋይናንስ ትምህርት አይነቶች ተደራሽ መሆን | በዲስትሪክት የሚመራ 100% አልተገለጸም | *ከ23ቱ 20ው ለ22-23 የዲስትሪክት ባህላዊ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ22-23 መርሀግብር ላይ ከተዘረዘሩት የትምህርት ዓይነቶች መካከል ቢያንስ የ 1 የትምህርት አይነት የ 1 ክፍል አላቸው። ከ23ቱ 3ቱ በአሁኑ ወቅት በ 22-23 መርሀግብራቸው ውስጥ ከስር ከተዘረዘሩት የትምህርት አይነቶች ውስጥ የትኛውም የላቸውም። በተጨማሪም፣ ከ13ቱ በዲስትሪክት የሚመሩ የኢኖቬሽን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9ኙ በዲስትሪክት 100% ከሚመሩት የ22-23 ኮርሶች ቢያንስ የ 1 የትምህርት አይነት የ 1 ክፍል አላቸው።* | |

## ማጠቃለያ

የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቡድንና እኔ በትክክለኛው የመመረቂያ መስመር (OTG) ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች መነሻ አዘጋጅተናል።
በቀጣይ መሻሻልን እንደ መቆጣጠሪያ የሚቀጥለውን ዓመት የተመራቂ ተማሪዎች መጠን (AYG) በጁን OTG መጠኖች አማካኝነት እከታተላለሁ። ከጁን 2022 ዓ.ም ጀምሮ 65% የAYG 2023 ተማሪዎች (በትምህርት ቤቶች ቤተሰብ ውስጥ በሙሉ) በትክክለኛው የውጤት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን 54% ተማሪዎች በትክክለኛው የብቃት ደረጃ ላይ ናቸው።

